VIRGINIA HOSPITAL CENTER

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ

የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ለታማሚዎቹ፣ የመክፈል አቅማቸው ምንም ይሁን ምንም፣ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት በሚሰጠው አትራፊ ባልሆነው የድርጅትነት ተልዕኮው፣ እንዲሁም ተልዕኮውን የሚፈፅመው ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለታማሚዎቹ ክብር እና ርህራሄ በማሳየት እና ስብዓዊነታቸውን በመጠበቅ በመሆኑ ኩራት ይሰማዋል።

የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት እዚህ ግብ ለመድረስ መድን ለሌላቸው ወይም መድናቸው በቂ ላልሆነ ህመምተኞች የሚሆኑ አግባብ ያላቸው("ኤሊጂብል") አገልግሎቶች (ትርጉሙ ከዚህ በታች እንደተበየነው) የገንዘብ እርዳታ የሚያመቻች መርሀ ግብር መስርቷል። በዚህ ፕሮግራም፣ ገቢያቸው ፌዴራል መንግስት ካሳተመው የድህነት መለኪያ 200 % በታች የሆነ ቤተሰብ ታማሚዎች፣ አግባብ ያላቸውን አገልግሎቶች፣ ("ኤሊጂብል ሰርቪስስ") ከኪሳቸው ሊከፈል የሚገባውን የክፍያ ድርሻ ሳይከፍሉ ነጻ ህክምና (የገንዘብ ድጋፍ) ያገኛሉ። የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ላይ ተመስርቶ እሴቱ / ጥራቱ የቀነሰ አገልግሎት አይሰጥም።

**ተጠቃሎ በቀላሉ ሊገባ በሚችል ቋንቋ የተፃፈ የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ እና እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ የመጠየቂያ ማመልከቻ ቅፅ www. virginiahospitalcenter.com/fap ላይ ይገኛል።**

## የገንዘብ ድጋፍን በሚመለከት ለታማሚዎች ማስታወቂያ

የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ፣ አለትርፍ ጥራት ያለው የጤና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ የመስጠት ተልእኮው ይኮራል።

ታካሚዎቻችን፣ ቤተሰቦቻቸው፣ እንዲሁም ሰፊው ማህበረሰብ፣ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራማችን መኖሩን እንዲገነዘቡ ለማድርግ በተደረገ ጥረት፣ልዩ ልዩ የሚነበቡ ማመላከቻዎች ፣ የተጠቃለለ እና በሚገባ ቋንቋ የተጻፈ የገንዘብ ድጋፉ ፖሊሲ ይዘት( "ፒ ኤል ኤስ") እንዲሁም መረጃዎች የያዙ በራሪ ወረቀቶች (“ፓምፍሌትስ") በሆስፒታላችን የመመዝገቢያ ስፍራ፣ በወረዳ የማህበራዊ አገልግሎት ጽ/ቤቶች፣ እንዲሁም በሌሎች በጎ አድራጊ ድርጅቶች ዘንድ ለማስራጨት የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት የተለያዩ እርምጃዎች ወስዷል። እነዚህ ፅሁፎች፣ ማለትም የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው፣ የዚሁ ፖሊሲ ማጠቃለያ እና የገንዝብ ድጋፍ መጠየቂያ ቅፁ፣ በእንግሊዝኛ እና በተለያዩ ሌሎች ቋንቋዎች ተጽፈው ይገኛሉ።

## የትርጉም ብያኔዎች

1. ***መድን የሌላቸው***

   *ታካሚው የክፍያ ግዴታውን እንዲወጣ የሚረዳ(ው)(ት) መድን ወይም የሌላ ሶስተኛ ወገን እርዳታ የለውም።*

2. **በቂ *መድን የሌለው***

   *ታካሚው በተወሰነ ደረጃ መድን ወይም የሶስተኛ ወገን እርዳታ አለው፣ ግን እንደዚያም ሆኖ፣ ከገቢው አቅም በላይ የሆነ ከኪሱ መክፈል ያለበት ወጭ አለ።*

3. ***የገንዘብ ድጋፍ***

ድጋፍ የሚሰጠው (ከታች እንደተገለፀው) አግባብነት ላላቸው ("ኤሊጂብል") አገልግሎቶች ነው። እርዳታውን የሚያገኙትም የቤተሰብ ገቢያቸው ታትሞ ከወጣው የፌዴራል መንግስት የድህነት መለኪያ ከ 200% በታች የሆኑ እና ምንም መድን ወይም በቂ መድን የሌላቸው ህመምተኞች ነው። እንዲህ ዓይነቶች አግባብነት ያላቸው ("ኤሊጂብል")አገልግሎቶች በቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት የሚሰጡት ምንም ክፍያ ሳይጠበቅ ነው። የገንዘብ እርዳታው መሰብሰብ ያልቻለ ዕዳን ወይም ከመንግስት መርሀ ግብሮች ዘንድ የተፈጠረን እጥረትን አያካትትም። ሆኖም መድን ከህመምተኞች የሚጠይቀውን ክፍያ ("ኮ-ፔይ") ወይም ኢንሹራንስ ከመክፈሉ በፊት በህመምተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎችን ("ዲደክተብልስ") ወይም ሁለቱንም ሊያካትት ይችላል። አባክዎ፣ በቪርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መርሀ ግብር የመድን አረቦን ("ፖሊሲ") **አለመሆኑን** ይገንዘቡ።

4. ***አግባብነት ያላቸው ("ኤሊጂብል") አገልግሎቶች***

በሆስፒታሉ የሚሰጡ ለገንዘብ ድጋፍ አግባብነት ያላቸው ("ኤሊጂብል") አገልግሎቶች ሚያካትቱት፡ (1) በድንገተኛ ህክምና መስጫ ስፍራ የሚሰጡ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶችን፤ (2) የድንገተኛ ህክምና መስጫ ባልሆኑ ስፍራዎች ሕይወትን ላደጋ በሚያጋልጡ ሁኔታዎች ምክንያት የሚሰጡ ቅድመ ምርጫ ያልተደረገባቸው ("ነን ኢሌክቲቭ") አገልግሎቶችን ፤ (3) በጤና እንክብካቤ ሰጭው አካል ፤ የታካሚውን ገቢ ግንዛቤ ውስጥ ባላስገባ "ክሊኒካል" ግምገማ መሰረት፣ የግድ ህክምና የሚያስፈልጋቸው (ከዚህ በታች እንደተተረጎመው) የጤና ጉዳዮችን ነው።

5. ***የግድ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው የጤና ጉዳዮች***

**ትርጉሙ በሜዲኬር እንደተበየነው** -ህመምን/ በሽታን ወይም ጉዳትን መርምሮ ለማወቅ ወይም ለማከም ተገቢ እና በአእምሮ ግምት አስፈላጊ የሆኑ የጤና አግልግሎቶች ወይም አቅርቦቶች።

6. ***የተካተቱ አገልግሎት ሰጭዎች***

የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው በ"ቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር" በቀጥታ በተቀጠሩ ሐኪሞች የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል። የድንገተኛ ሐኪሞች፣ አደንዛዦች፣ ሬዲዮሎጂስቶች እና ፓቶሎጂስቶችን ጨምሮ፣ራሳቸውን ችለው እንደ ተዋዋይ ለቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት አገልግሎት የሚሰጡ ሐኪሞች ላይ ተፈፃሚነት የለውም። ራሱን ችሎ ከሚተዳደር ሐኪም ወይም ለቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ራሱን እንደቻለ ሐኪም አገልግሎት የሚሰጥ መስሎ ተግባሩን ከሚያከናውን ሐኪም የክፍያ ጥያቄ ከደረሰዎት፣ ለተሰጥዎት አገልግሎት መከፈል የሚገባውን ክፍያና የክፍያ አፈፃፀሙን በሚመለከት ለመወያየት ከነዚሁ ሐኪሞች ጽ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ማድረግ አለብዎ። አንድ ሐኪም በቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ተቀጥሮ የሚሰራ ስለመሆኑና ስላለመሆኑ ጥያቄ ካለዎት አባክዎ ወደ ሆስፒታሉ የምዝገባ ክፍል ቀርበው ይጠይቁ ወይም በስልክ ቁጥር 703.558.2492 ወደ የገንዘብ እርዳታ መምሪያ ይደውሉ።

7. ***መሰብሰብ የማይቻል ውዝፍ ዕዳ***

ለመክፈል የሚያስፈልገው የገንዘብ ክምችት ያላቸው በመሆኑ ምክንያት ለገንዘብ ድጋፍ ለማይመጥኑ እና በድርጊታቸው ከውል የሚመነጭ ዕዳን ለመክፈል ፍቃደኛ ላልሆኑ ታካሚዎች ወይም/ እና ዋሶች ከተሰጠ የሕክምና አግለግሎት የሚመነጭ ወጭ።

8. ***ቤተሰብ***

በህዝብ ቆጠራ ቢሮ በተበየነው ትርጉም መሰረት ከሁለት በላይ የሆኑና አብረው የሚኖሩ፣ በመወለድ፣ በጋብቻ ወይም በጉዲፈቻ የሚዛመዱ ስብስቦች። በሀገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ደንቦች መሰረት አንድ ታካሚ፣ ታክስ በሚከፍልበት ጊዜ፣ አንድን ሰው ጥገኛዬ ነው ብሎ ካስገባ፣የገንዘብ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ እንደ ጥገኞች ሊቆጠሩ ይችላሉ።

## መርህዎች

1. **የገንዘብ ድጋፍ ድንጋጌዎች**
   በዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ መሰረት አግባብነት ("ኤሊጂቢሊቲ") ያላቸው አገልግሎቶች ሁሉ ለሁሉም ግለሰቦች ይሰጣሉ። የተጠቃለለውን የዚሁ ፖሊሲ ሰነድ እና የገንዘብ እርዳታ መጠየቂያ ማመልከቻ ቅፁን ኮፒዎች በድንገተኛ መምሪያው መመዝገቢያው ክፍል፣ በሆስፒታሉ የቅበላ (አድሚሽንስ ) አካባቢ፣ በዋናው መጠበቂያ ክፍል በሚገኘው የእንግዳ ተቀባዩ ጠረጴዛ ዘንድ ወይም ከሆስፒታሉ ድረ ገፅ ላይ በነጻ ያገኛሉ። አንድ ታካሚ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያበቁ ሁኔታዎችን ያሟላል አያሟላም የሚለው ውሳኔ በተቻለ ፍጥነት ይሰጣል፤ ሲሆን ሲሆን ከሆስፒታሉ እንዲወጣ ከመደረጉ በፊት። በምንም ምክንያት ቢሆን ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆኑ የተረጋገጠለት ሰው የክፍያ መጠየቂያ (ቢል) ሰነድ አይወጣበትም።

2. **ያለማዳላት**
   የማንኛውም ታካሚ የመታከም አስፈላጊነቱ የሚወሰነው ፣ የታማሚውን የገንዘብ ገቢ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማያስገባ የጤና አገልግሎት ሰጭ "ክሊኒካል" ውሳኔ ላይ ተመስርቶ ይሆናል። ታካሚዎች ሁሉ፣ ለገንዘብ አርዳታ ብቁ ሆኑም አልሆኑም፣ አግባብነት ያላቸው ("ኤሊጂብል") አገልግሎቶችን በማግኘት ረገድ አንዳችም አድልዎ አይደረግባቸውም። የገንዘብ እርዳታው በታካሚው የመክፈል አቅም ላይ የሚመሰረት ይሆናል እንጂ የግለሰቡ እድሜ፣ ፆታ፣ ዘር፣ ሃይማኖት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ወሲባዊ አመለካከት ("ሴክሽዋል ኦርዬንቴሽን") የትዳር ሁኔታ፣ የጥገኝነት ሁኔታ ወይም የብሔር ምንጩ ውጤቱ ላይ ተፅእኖ አያደርግም።

3. **ማመልከቻ የሞሙላት እርዳታ**
   የሆስፒታሉ የገንዘብ ነክ ጉዳዮች አማካሪዎች እና የአርሊንግተን ወረዳ ስራተኞች፣ ታካሚዎች ለወረዳ፣ ለስቴት ወይም ፌዴራል የእርዳታ መርሃ ግብሮች፣ (ሜዲኬድን፣ የድንገተኛ ሜዲኬድን፣ የአካል ጉዳተኝነት ኤስ ኤስ አይን እና ኤስ ኤል ኤችን ጨምሮ፣ ነገር ግን በነርሱ ብቻ ሳይገደብ፣) ማመልከቻ በሚያስገቡበት ጊዜ፣ እርዳታ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

4. **የታካሚ ሃላፊነት**
   ከዚህ በታች በዝርዝር እንደተገለፀው፣ የገንዘብ ድጋፉን ለማግኘት ፣ ታካሚዎች ትብብር ያደርጋሉ፣ እንዲሁም አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በወቅቱ ለቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ ማመልከቻ ማስገባት

ታካሚዎች ከሆስፒታል ሲወጡ የሚዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ከደረሳቸው በኋላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ለማስገባት 240 ቀናት አሏቸው። ማንም ሰው የማመልከቻ ቅፁን በመሙላት እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች በማቅረብ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፡

- ሁለት የቅርብ ጊዜ የገቢ ቼክ ተቆራጭ ቀሪዎች ወይም ግብር የተከፈለባቸው ቅፆች ኮፒዎች
- የቤት ኪራይ ውል ኮፒ (አግባብነት ካለው)
- የቅርብ ጊዜ የባንክ ሂሳብ መግለጫዎች ኮፒዎች

ታካሚዎች በቨርጂንያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ሕክምና በሚያገኙበት ወቅት የማመልከቻ ቅጹንም እዚያው ያገኛሉ። የማመልከቻ ቅፁን፣ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን እና በቀላል ቋንቋ ባጭሩ ተጠቃሎ የተዘጋጀውን ሰነድ ከ www.virginiahospitalcenter.com/fap ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም አብረው የሚገኙ የአሞላል መመሪያዎችም፣ ብቁነትን ለመወሰን ምን ምን ሰነዶች እንደሚያስፈልጉ በመግለፅ፣ ቅፁን በመሙላት ረገድ ታካሚዎችን ይረዳሉ።

እንዳማራጭ ደግሞ፣ የሆስፒታሉን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ፣ በሚገባ ቋንቋ ባጭሩ የተጠቃለለውን ሰነድ እና የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ የማመልከቻ ቅፁን፣ በዋናው መቀበያ ክፍል ውስጥ ያለውን የእንግዳ ተቀባዩን ቦታ ጨምሮ፣ በሆስፒታሉ የመመዝገቢያ ስፍራዎች ዘንድ በህትመት መልክ በነፃ ሊገኙ ይችላሉ። ነፃ ኮፒ በፖስታ

እንዲላክላችሁ ለገንዘብ ድጋፍ መምሪያ በ 703.558.2492 ስልክ መደወል ትችላላችሁ።

የተሞላው የማመልከቻ ቅፅ እና ደጋፊ ሰነዶቹ በሙሉ ለሚከተለው አድራሻ መላክ አለባቸው:

Virginia Hospital Center Business Office
Attention: Financial Assistance Department
2800 Shirlington Road, Suite 600
Arlington, VA  22206

## የብቁነት አወሳሰን

አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ፣ የታካሚውን የመድን ወይም የገቢ አቋም የሚያሳይ የተሟላ መረጃ ማግኘት ካልተቻለ፣ ወይም የገቢ አቋሙ ከተለወጠ፣ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነቱ አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ ሊወሰን ይችላል። ታካሚው ሆስፒታሉን ለቆ ከመውጣቱ በፊት ለገንዘብ እርዳታ ብቁ ነው አይደለም የሚለውን ለመወሰን አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ይደረጋል።

የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው የተለያየ ገቢ መጠን ላይ በተመሰረተ ደረጃ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን ገቢያቸው ከፌዴራል መንግስት የድህነት መመሪያዎች በ 200% ያነሰ የቤተሰብ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች ታካሚዎች በሙሉ ነፃ የጤና እንክብካቤ በመስጠት ነው። ለገንዘብ ድጋፉ ብቁ ሆኖ ለመገኘት የሚያስፈልገው የገቢ መጠን፣ በየወቅቱ በፌዴራል ሬጂስተር የሚታተመውን የፌደራል የድህነት መለኪያ መመሪያ በሚያንፀባርቅ መልኩ እንደገና በየዓመቱ ይሰላል።

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ የሚያሳየው ለ 2019 ስራ ላይ የዋለውን የፌዴራል የድህነት ደረጃ ነው:

| **የቤተሰብ ብዛት** | | **የድህነት መጠን መመሪያው** | **200%** |
|---|---|---|---|
| 1 | | $12,880 | $25,760 |
| 2 | | $17,420 | $34,840 |
| 3 | | $21,960 | $43,920 |
| 4 | | $26,500 | $53,000 |
| 5 | | $31,040 | $62,080 |
| 6 | | $35,580 | $71,160 |
| 7 | | $40,120 | $80,240 |
| 8 | | $44,660 | $89,320 |

**ማስታወሻ: ከስምንት ሰዎች በላይ ላቀፉ ቤተሰቦች ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ሰው  $4,540 ክል።**

## አሰራሮች

የልዩ ፕሮጀክቶች አስተባባሪያችን የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ቅፅ ሲደርሰው፣ የቀረበለትን መረጃ በ 30 ቀናት ውስጥ መርምሮ ብቃትን በሚመለከት ውሳኔ ላይ ይደርሳል። ታካሚው ፣ በመጀመሪያ ከሆስፒታል ሲወጣ የሚሰጠው የሂሳብ መግለጫ በተሰራ በ 240 ቀናት ውስጥ የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ቅፅ እስኪያስገባ ወይም "ፕሬዘምቲቭ ቻሪቲ ኬር" (ከዚህ በታች እንደተገለፀው) እስኪያገኝ ድረስ እንደ ከፋይ ታካሚ የሚታይ ይሆናል።

ግዴታ ባይሆንም፣ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄው እና በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ መሰረት የሚሰጠው የብቃት ውሳኔ አግባብነት ያላቸው ("ኤሊጂብል") አገልግሎቶቹ ከመሰጠታቸው በፊት ቢሆን ይመረጣል። ይሁንና የብቃት ውሳኔ በምዝገባ ወቅት፣ ሕክምና በሚካሄድበት ወቅት፣ ወይም በሂሳብ መተሳሰቡ ሂደት ወቅት ሊሰጥ ይችላል። የፀደቁ የገንዘብ እርዳታ ማመልከቻዎች ለስድስት ወራት ጊዜ ፀንተው ይቆያሉ።

## ያልተሟሉ ማመልከቻዎች

አንድ ታካሚ ያልተሟላ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ካስገባ (ማለትም መረጃን በሚመለከት ወይም ሰነዶችን በሚመለከት) የጎደለውን መረጃ ወይም ሰነድ እንዲያሟላ ለመጠየቅ የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ከታካሚው ጋር ግንኙነት ያደርጋል። ታካሚው ተፈልጎ በማይገኝበት ጊዜ፣ ወይም ምላሽ የማይሰጥ ወይም የተጠየቀውን የማይፈፅም ሆኖ ከተገኘ፣ ሆስፒታሉ የግለሰቡን ሂሳብ በራስ እንደሚከፈል ሂሳብ አድርጎ በመቁጠር ዕዳ ሰብሳቢ ድርጅቶች ቀጣዩን እርምጃ እንዲወስዱ ከማስተላለፉ በፊት፣ግለሰቡን ለማግኘት ሙከራ ከተጀመረበት ጀምሮ በአእምሮ ግምት በቂ ነው ሊባል ለሚችል ጊዜ ይጠብቃል። ይኽ ቢሆንም፣ ማንኛውም ታካሚ፣ የመጀመሪያው ከሆስፒታል ሲወጡ የሚዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ በ 240 ቀናት ውስጥ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጠው አሁንም ማመልከት ይችላል።

***ማመልከቻውን ለመሙላት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች ለገንዘብ እርዳታ መምሪያ በስልክ ቁጥር 703.558.2492 መደወል ወይም ከዚህ በታች ከሰፈረው አድራሻ ዘንድ ሂደው መጠየቅ ይችላሉ።***

Virginia Hospital Center Business Office
Financial Assistance Department
2800 Shirlington Road, Suite 600
Arlington, VA 22206

## “ፕሬዘምፕቲቭ ቻሪቲ ኬር”

አንዳንድ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ቅፅ አሟልቶ ለመሙላት፣ የተጠየቁትን ሰነዶች አሟልቶ ለማቅረብ ወይም ደግሞ ማመልከቻ ለማቅረብ ሂደቱ ምላሽ ለመስጠት የማይችሉ መሆኑን የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ይገነዘባል። በዚህም ምክንያት የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ቅፁ ተሟልቶ ሳይገባ ታካሚው የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ያለው ብቃት ሊረጋገጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣ የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት የታካሚውን የገንዘብ ድጋፍ ፍላጎት መጠን ለመገምገም በተለያዩ የመረጃ ምንጮች ሊገለገል ይችላል። ከታካሚው በቀጥታ የቀረበ መረጃ በሌለበት ሁኔታ በዚህ መልክ የሚገኘው መረጃ፣ ልናገኝ በቻልናቸው የተሻሉ መረጃዎች ላይ ተመርኩዘን ምላሽ መስጠት የማይችሉ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ፍላጎት መጠን ላይ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ መስጠት እንችላለን።

የታካሚውን የገንዘብ ድጋፍ ፍላጎት መጠን ለመገምገም፣ ሆስፒታሉ የ"ኤሌክትሮኒክ" ዳሰሳ እንዲያካሂድለት በሶስተኛ ወገን መገልገል ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ዳሰሳ በጤና ኢንዱስትሪው ተቀባይነት ባገኙ የ "ፐብሊክ" የመረጃ ቋቶች (“ዳታ ቤዞች") ላይ በተመሰረተ ሞዴል ይገለገላል።ይኽ የትንበያ ሞዴል፣ የገቢ፣ የንብረት እና የ"ሊኩዲቲ" ግምቶችን የሚጨምር የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ መለኪያዎችን ለማስላት፣ የ"ፐብሊክ" መረጃዎችን ያካትታል።

የ”ኤልክትሮኒክ" ቴክኖሎጂው እያንዳንዱን ታካሚ በተመሳሳይ ደረጃ ለመገምገም የተነደፈ ከመሆኑም በላይ በተለመደው የማመልከቻ ሂደት መሰረት ከሆስፒታሉ የገንዘብ እርዳታ እንዲገኝ ከዚህ ቀደም ከተደረጉ ውሳኔዎች ጋርም እንዲጣጣም ("ካሊብሬት") ይደረጋል።

የ"ኤሌክትሮኒክ" ቴክኖሎጂው አገልግሎት ላይ የሚውለው ሊከፈል ያልቻል ዕዳ እንዲሰበሰብ ከመዳረጉ በፊት፣ ነገር ግን ሁሉም ዓይነቶች የብቃት እና የክፍያ ምንጮች ተሞክረው ካበቁ በኋላ ነው። ይኽ አካሄድ፣ ሆስፒታሉ ልዩ ያልተከፈለ ዕዳ የመሰብሰብ እርምጃ ("ኢሲኤ") ከመውሰዱ በፊት፣ ሁሉንም ታካሚዎች ከገንዘብ ድጋፍ ፍላጎታቸው መጠን አኳያ ለማጣራት ያስችለዋል። ከዚህ የ"አሌክትሮኒክ" የብቃት ዳሰሳ የሚገኘው መረጃ በፖሊሰው መሰረት አጥጋቢ የገንዘብ ድጋፍ ፍላጎት መጠን ማስረጃ ሰነድ ሆኖ ይቆጠራል።

**አንድ ታካሚ በ”አሌክትሮኒኩ" የምዝገባ ("ኤንሮልሜንት") ሂደት ብቁ ሆኖ ባይገኝም በተለመደው የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ሂደት መሰረት እንደገና ሊታይለት ይችላል።**

የ"ፕሪዘምፕቲቭ ኤሊጂቢሊቲ" ደረጃ የተሰጣቸው የታካሚ ሂሳቦች፣ በገንዝብ ድጋፍ ፖሊሲው ስር (መሰረት) እንደገና ይመደባሉ። ወደ ውዝፍ ሂሳብ ሰብሳቢ አይላኩም። ተጨማሪ የውዝፍ ዕዳ የመሰብሰብ አርምጃ ውስጥ አይካተቱም። ሰላመዳደባቸው እንዲያውቁ አይደረግም። እንዲሁም በሆስፒታሉ የውዝፍ ዕዳ ኪሳራ ውስጥ አይካተቱም።

## የውዝፍ ዕዳ አሰባሰብ ፖሊሲ

የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ውዝፍ እዳ አሰባሰብ ፖሊሲ፣ ታካሚው ለገንዝብ ድጋፍ ያለው ብቃት ምን ያኽል እንደሆነ እና ታካሚው በድርድር ሊከፍለው በገባው የክፍያ ዕቅድ ግዴታ መሰረት ለመፈፀም የሚያደርገውን የቅንነት ጥረት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል።

> ታካሚው ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ካልሆነ፣ በቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት እና በሌሎች በሚሸፈኑ የጤና እንክብካቤ ሰጭዎች ለተሰጡት አገልግሎቶች መፈፀም ያለባቸው ክፍያዎች በ 30 ቀናት ውስጥ ተከፋይ ናቸው። ሆኖም ታካሚው ለ 120 ቀናት ወርሃዊ የክፍያ መጠየቂያዎች ሲደርሱት ይቆያሉ። ታካሚው ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ እና ተቀባይነት ያለው የክፍያ አፈፃፀም ስምምነት ለማድረግ ከቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ጋር ግንኙነት ካላደረገ፣ የታካሚው ሂሳብ ወደ ባለሞያ የውዝፍ ዕዳ ሰብሳቢ ድርጅት ይተላለፋል። በአእምሮ ግምት በቂ ከሆነ ጊዜ በላይ ክፍያ ያለመፈፀሙ ሁኔታ ከቀጠለ፣ ውዝፍ ዕዳውን ለመሰብሰብ የውዝፍ ዕዳ ሰብሳቢው ድርጅት ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። ከቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት ጋር ከተዋዋሉት ውዝፍ ሰበሳቢ ድርጅቶች ጋር በተደረገው የውዝፍ አሰባሰብ ስምምነት መሰረት፣ እነዚህ ውዝፍ ሰብሳቢ ድርጅቶች፣ ሕጋዊ እርምጃ ከመውሰዳቸው ቢያንስ ከ 30 ቀናት በፊት፣ ለታካሚው በቂ ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ። የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን ዓላማ በተመለከተ ከዚህ በታች የሚዘረዘሩት እርምጃዎች ኢ ሲ ኤ እንደሆኑ ተደርጎ ይቆጠራል፡

- ያንድን ግለሰብ እዳ ለሌላ መሸጥ፣
- ግለሰብን የሚጎዱ መረጃዎች ለሸማቾች ክሬዲት ዘጋቢ ድርጅቶች ወይም ለክሬዲት ቢሮዎች መዘገብ፣
- ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ፣ ህጋዊ ወይም የዳኝነት አርምጃ የሚጠይቁ ድርጊቶች፡
    - o በግለሰብ ንብረት ላይ የዕዳ እግድ፣
    - o በግለሰብ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሐራጅ እርምጃ ፣
    - o የግለሰቡን ባንክ ሂሳብ ወይም ሌላ የግል ንብረት በእዳ መያዝ ፣
    - o በግለሰቡ ላይ የፍትሀ ብሔር ክስ መመስረት ፣
    - o ግለ ሰብ እንዲታሰር ማድረግ ፣
    - o ግለሰቡ የፍርድ ቤት መጥሪያ እንዲወጣበት ማድረግ ፣
    - o ከግለሰብ ደሞዝ ላይ ተቆራጭ ማድረግ ።

የቨርጂኒያ ሆስፒታል ሴንተር የጤና ሥርዓት፣ በታካሚ ያልተከፈለ ሂሳብ ላይ፣ በታካሚው ያከፋፈል ሁኔታ፣ ወይም ከታካሚው ውዝፍ ዕዳ ለመሰብስብ ቀደም ብለው በሆስፒታሉ በተወሰዱ አርምጃዎች፣ ላይ ተመርኩዞ አግባብነት ያለው የጤና አገልግሎት አይነሳም ወይም አያዘገይም።

## የተከፈለ ገንዘብ የመመለስ ፖሊሲ

የሕክምና ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ታካሚውን በሚመለከት የገንዝብ ድጋፍ የማግኘት ብቃት ውሳኔ ከተሰጠ፣ በታካሚው የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ መጠየቂያ ቅፅ ላይ ለተመለከቱ የጤና አገልግሎቶች የተደረጉ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

**የገንዘብ እርዳታ ፖሊሲያችንን በሚመለከት ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም የገንዘብ እርዳታ ማመልከቻውን ለመሙላት ድጋፍ ካስፈለገዎ፣ እባክዎ ለገንዘብ ድጋፍ ምመሪያችን በስልክ ቁጥር 703.558.2492 ይደውሉ፣ ወይም ከዚህ በታች እሰፈረው አድራሻ ድረስ ይምጡ፡**

Virginia Hospital Center Business Office
2800 Shirlington Road, Suite 600
Arlington, VA  22206

እርሰዎን እና ጥያቄዎችዎን በትህትና፣ ባክብሮት እና በሚስጥር እንይዛለን።

የፀደቀው በ: ______________________________

ቀን:____________________________________